# የኣእምሮ ዝቀት ወይስ የእድገት ፖለቲካ

ሓጎስ ኣረጋይ (PhD) 4/12/2009

ኣገራችን ረዥም ግዜ ያስቆጠረ የፖለቲካዊ ምህዋር (እንደ ኣገር) ባለቤት መሆንዋን የሚያከራክር ኣይመስለኝም። የኣክሱምን ዘመነ መንግስት ብንወስድ በወቅቱ በስልጣኔ ማማ ላይ እንደነበርን ታሪካዊ ኣሻራዎቻችን ህያው ምስክሮች ናቸው። ነገር ግን ከ1270ዓ/ም ጀምሮ ለ700 (1270-1966) ዓመታት ያህል የፖለቲካ ምህዋሩ ከእምነት ጋር በመቆራኘቱ የኣመራሩ ኣካላት በእምነት ስር ተጠልለው ለብዙ ዘመናት መቆየታቸው ይታወቃል። በዚህ የፖለቲካ ምህዋር ለስልጣኔ በር ከፋች የሆነውን የእደ ጥበብ ስራዎች በማንቋሸሸቸው ህዝባችን ከእድገትና ብልፅግና ርቆ ቆይተዋል። ይህን በተመለከተ የዴሞክራሲና የባህል ጎዞ በኢትዮጵያ በሚል ርእስ ሰኔ 21/ 2009 ላይ በኣይጋ ፎሮም ፖስት ተደርግዋልና ዝርዝሩን መመልከት ይቻላል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝቦች በስልጣኔ የነብራቸው የቀዳሚነት ስፍራ ለቀው በኣለማችን ከሚገኙ ኣገራት መካከል ውስጥ የጭራ ጭራ ሁነን ቆይተናል። ጭራ ብቻ ሳይሆን ሁለኣቀፍ የኋልዮሽ ጉዞ ተያይዘነው ነበር ማለት ይቻላል። መገለጫውም ረሃብ፣ ቸነፈር፣ ኋላቀርነት በኛ ላይ ኣንዠብበውና ስጦታችን ሁነው እንደነበር በኢንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ famine የሚለውን በኢትዮጵያ ተመስሎ ቀርቦ እንደነበር የቅርብ ትዝታችን ነው ። የችግራችን ብዛት የወሎ ረሃብ እንኳን ማስታገስ ኣለመቻላችን በድህነት ኣለም ውስጥ ዝቅጠታችን ገሃድ ያደርገዋል። በእርግጥ በዚያን ወቅት እንደኣሁኑ ግዜ የየእለት ተግባራትን መዘገብ ቢቻል ኑሮ ብዙ ጉድ ይወጣ ነበር በዬ ኣስባሎህ።

በችግሩ የተማረረው የኢትዮጵያ ህዝብ ፣ የዘውዳዊን ኣገዛዝ ለመጣል በ1966 የማያቋርጥ የለውጥ ማእበል ውስጥ ገባ። ነገር ግን የለውጡ ማእበል በዘውዳዊው ስርዓት መልዮ ለባሾች በመጠለፉ ዳግም ለሰቆቃና ለእንግልት ተዳረግን ። በመሆኑም ሌላ ኣማራጭ መከተል ግድ ስለነበር የለውጥ እንቅስቃሴው ሳያቋርጥ ደርግን ለማንበርከክ በኣገሪቱ የተለያዩ ወገኖች (ፖለቲካ ድርጅቶች) የትጥቅ ትግል ማካሄድ ጀመሩ። እንደየፊናቸውም በኣገሪቱ የነበረውን ነባራዊና መፃኢ ሁኔታ በመተንተን የየራሳቸው ኣጀንዳ ማስረፅ ጀመሩ ። ከፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ኢድህ፣ ኢህኣፓ ህወሓት የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል ። በሂደተም ኣንዳንድ ፓለቲካ ድርጅቶች እየጎለበቱ ሲሄዱ ሌሎች ግን እየከሰሙ በመሄዳቸው ለስደት ተዳረጉ።

በዚህ እልህ ኣስጨራሽ የነበረውን የትግል ሂደት ውስጥ ፣ የፖለቲካ ድርጅቶችን መልሶ የመደራጀት እንዲሁም ራእያቸው ዳግም በመከለስ አስተካከለውና ኣደራጅተው በመንቀሳቀስ የኢትዮጵያ ህዝቦች ኣብዮታዊ ዴሞክሲያዊ ግንባር (ኢህኣዴግ) የሚል ፓለቲካ ድርጅት መሰረቱ። በመሆኑም ደርግንና የዘውዳዊው ኣስተሳሰብ ለኣንዴና ለመጨረሻ ግብዓተ መሬት እንዲገቡ ሆነ። ቀጥሎም ፣ በዘውዳዊና በደርግ ፈላጭ ቆራጭ ኣገዛዝ የበላይነት ይዘው የነበሩ እንደ፣

- የህዝብን መብት ኣግልለው የግዛት ኣንድነትን ላይ የመጨነቅን ኣስተሳሰብ ኣበቃለት
- ብሄራዊና የመደብ ጭቆና ከስር መሰረቱ ተደመሰሰ
- ከላይ እስከታች በእንደ ራሴ ተወጥሮ የነበረውን የኣስተዳደር ሰንሰለት ከስር መሰረቱ ተገረሰሰ

በምትኩ ደግሞ ሁሉም ብሄር ብሄረ ሰቦች በእኩል የሚታዩባትን ኣገር የመመስረት ጉዳይ ኣንድ ተብሎ ተጀመረ። ከሁሉም በፊት ተግባራዊ የሆነው ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን ሙሉ በሙሉ የማረጋጥ ጉዳይ ነው። በመሆኑም የክልል

መንግስታት ተጠሪነታቸው ለየክልሉ የህዝብ ተውካዮች ም/ቤት እንዲሆን ተደረገ። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ መንግስት ለመጀመርያ ግዜ በሚባል መልኩ ተዋቀረ። በዚህ ኣኳሃን የክልል መንግስታት የስልጣን ኣወቃቀር የሚያሳየው በቀጥታ ከበላይ የሚያዝ ኣካል ኣለመኖሩን ገሃድ ያደርገዋል። ይልቁንስ የፌደራል መንግስት ከክልል መንግስታት በውክልና የሚቋቋም መንግስታዊ ስልጣን መሆኑን ያበስራል ። እየህነ ያለውም ይህ ነው።

ከላይ በተገለፀው መርህ መሰረት ክልሎች በየክልላቸው ያለው የፀጥታ፣ የማህበራዊ (ጤንነት፣ትምህርትወዘተ) ፣ የፍትህ፣ የኣስተዳደር ጉዳዮች በሙሉ ሃላፊነት ወሰደዋል እየተተገበረ ያለውም ይህ ነው። ስለዚህ የክልል መንግስታት የየክልሉ የህዝብ ወኪሎችና በህዝብ የሚመረጡ ናቸው። በመሆኑም ኣንዱ ክልል በሌላኛው ጣልቃ የመግባት ስልጣን በፍፁም ኣይደረግም የህግ ማቀፍም የለውም። ምክንያቱም ለዚያ ክልል የስልጣን ባለቤት ኣይደለም። በመሆኑም ህወሓት እንደ ፓርቲ የተመረጠው በትግራይ ህዝብ ነው። ውክልናውም ለትግራይ ህዝብ ነው የሚሆነው። ስለዚህ ህወሓትን ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ የሚችለው የትግራይና የትግራይ ህዝብ ብቻ እንጂ የኣማራ ህዝብ ሙብት ኣይደለም ። በተመሳሳይ መልኩ የኣማራ ህዝብ ብኣዴንን ከፍ ወይም ዝቅ ማድረግ ይችላል እንጂ የትግራይ ወይም የሌላው ክልል ህዝብ ሙብት ኣለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። የሁላችንም ድምር ውጤት የኣንድ ኣገር ይሆናል ማለት ነው። ለዚህም ሁሉም ብሄር ብሄረ ሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር ባለሙብቶችና ባለቤቶች መሆናቸውን በኢትዮጵያ ለመረጋገጥ ችለዋል። በመሆኑም ስለ ኣንድነት ኣንዱን ሌላውን የሚገት ሳይሆን የሁሉም ብሄር ብሄረ ሰቦች ኣጀንዳ መሆን ጀምረዋል ፣ እየተተገበረ ያለውም ይህ ነው።

በክልሎች ያለው የመንግስት መዋቅር ለማየት ሞክሪኣሎህ። በፌዴራል ደረጃ ያለው ኣካል ደግሞ ከየክልሎቹ የተውጣጣና በውክልና የሚሰራ ነው ። በመሆኑም የፌዴራል መንግስት ብለን እንጠራዋለን ። የፌዴራል መንግስቱ ተግባርም በህገ መንግስት የተቀመጥቱን መርሆዎች እንደ ኣገር ሁሉንም ክልኦች ባማከለ መልኩ ስራዎችን ያስፈፀማል ።

በፌዴራል ደረጃ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ያለው የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንደሆነ ህገ መንግስቱ በግልፅ ኣስቀምጠዋል። የምክር ቤቱ ኣባላትም ከየክልሉ የህዝብን ብዛት ማእከል ኣድርጎ የተመጣጠነ ውክልና ያለው ኣካል ሁኖ ተቋቁመዋል ። ለምሳሌ በም/ቤቱ የሚገኙ የትግራይና የኣማራን ክልሎች ተውካዮች ስንመለከት የትግራይ 38 ኣባላት ያሉት ሲሆኑ የኣማራ ደግሞ 138 ናቸው ። ም/ቤቱ ከፍተኛ የፌደራል የመንግስት ሹማሙንቶችን፣ ኣገራዊ ኣዋጆችን ፣ የኣገሪቱ በጀትን፣ ኣለም ኣቀፍ ስምምነትን ወዘተ ያፀድቃል። በም/ቤቱ የተሾሙ ከፍተኛ ባለስልጣናት ደግሞ በስራቸው ያለውን የሰው ሃይል በሚያወጡት መስፈርት መሰረተ ይሾማሉ ወይም ይቀጥራሉ።

ብናምንም ባናምንም በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ከላይ የተገለፀው መንግስታዊ መዋቅር ነው ያለው። በእንደዚህ የመሰለ የመንግስት መሳልል ውስጥ እያለን፣ በኣማራ ክልል ውስጥ፥

- የኣማራ ክልል ተወላጅ የሆነው ዜጋ ወያኔ ነው ሙብት ያሳጣው፣ ፍትህ ያሳጣው ፣የገደለው ፣ ቤቱ ያሸገው፣ ንግድ ፍቃዱ የሰረዘው ወዘተ ተብሎ ቢወራ ምኑ ላይ ነው እውነትነትን ኣለው ብለን ለሰከንድ እንኳን ማሰብ የምንችለው!!!
- ወያኔ በኣማራዎች የዘር ማጥፋት ስራ እየሰራ ነው ይላሉ፣ ሴቶች መካን እንዲሆኑ ይሰራሉ ወዘተ
- ካለው ኣንጡራ ሃብት ወደ ትግራይ የሚያጓጉዘው ወያኔ ተብሎ ቢወራ ምኑ ላይ ነው እውነትነት ኣለው ብለን የምናስበው ። እዚህ ላይ ኣንድ ነገር ላጫውታችሁ፣

**በጎንደር ከተማ ውስጥ  የውሃ የብረት ቱቦ መስመር   በፕላስቲክ  እየተቀየረ ነበር። ከዚያ በኋላ አንድ ግለሰብ ያሉትን ላውራችሁ ። መስመሩ በፕላስቲክ ቱቦ የመቀየሩ ጉዳይ የውሃ የብረት ቱቦ ወደ ትግራይ ለመውሰድ ፈልገው ነው ብለው እርፍ አሉ ብሎ አንድ ሰው አጫወተኝና ሁኔታው በምን ደረጃ እንዳለ ለማሰብ እድል ይሰጣል። በጣም የሚገርም አባባል ነው!!! ከዚህ በተጨማሪ** ሰሙኑ በዘሃበሻ የተነገረውን ላውራችሁ። ወደ ሰባት የኢለክትሪክ ጀኔረተር ( ከጎንደር፣ ባህርዳር፣ ጎጃም ወዘተ ) ወደ ትግራይ መጓጓዙን ያትታል። ማውራት ነው እንጂ በቂ ማስረጃ ግን አያስቀምጥም

- ***ውሃ በማይቋጥርና  ነገ ቢገልጥ የማያዛልቅ ትርክት ላይ ለምንድነው  የሚዘፈቁት? ለምንድነው ውሸት የሚፅፉት? ፋይዳ አለውን?  የሚሉ ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው የሚመስለኝ።***

በኔ  ግምት የሌለ ነገር እንዳለ አድርጎ በመሳልና  በማስመሰል፣ እንዲሁም ፈጥሮ በማውራት ላይ  የሚደረገው መውተርተር በአማራና በትግራይ ህዝቦች  መካከል ልዩነት እንዲፈጠር ማድረግ እንደሆነ እገነዘባሎህ ። የመጨረሻ ግቡም በህዝቦች መከካል ቅራኔና ግጭት ለመፍጠር የታለመም ይመስላል።  በቅራኔው ምክንያት  የሚፈጠረውን ክፍተት  ተጥቅሞ  ወደ ስልጣን መወጣቻ ብቸኛ አማራጭ  መንገድ አድርገው የወሰዱም ይመስላሉ ።

***ከላይ የተገለፀውን መላ ምት  በ2008 ዓ/ም ላይ ማቆራኘት ይቻላል። የአማራ ተወላጆች ሁነው  በሚናፈሰው ወሬ ተመርዘው  በጎንደርና በጎጃም አካባቢ በትግራይ ተውላጆች ላይ እጅግ የሚሰቀጥጥ ጉዳት አድርሰዋል።  የትግራይ ተወላጆች የሆኑ ሰዎች ቤታቸው ውስጥ እያሉ  የተቃጠሉ አሉ፣ ታድነው የተደበደቡና የተገደሉም አሉ ፣ ንብረታቸው የተዘረፈና የተቃጠለ እንዳለም እናውቃለን። ይህን ድርጊት በመፈፀማቸው ምክንያት   ሰሙኑን የጅግንነትን ቀን ለማስታወስ  እያሉ  የተለያዩ መጣጥፎች በዘሃበሻ ደህረ ገፅ በማስነበብ ላይ ናቸው ። ይገርማል በአካባቢው በሰላም በሚኖሩ  የትግራይ ተውላጆችን፣  በማንነታቸው ብቻ  ተመስርተው በፈፀሙት ጥፋትና ባደረሱት ፍፁም  ኣረሜናዊ  ግፍ  ጀግንነት ከሆነ በእርግጥ ያሳስባል። መልሰን መላልሰን ማየት ያለብን ይመስለኛል። እነዚህ ሰዎች ነገ  ወዲያ እድሉ ቢያገኙ በደርግ  መንግስት በሃውዜን እንዲሁም በመላ ትግራይ በናባል ቦምብ፣ በቤም፣ ታንክ፣ ኣውሮፕላን ተጠቅሞ በህዝባችን ያደረሰውን በደልና  የፈፀመውን ጭፍጨፋ እንደድል  ሊቆጥሩት እንደሆነ ጉልህ ማሳያችን  ነው።***

በ2008 ዓ/ም  በጎንደርና በባህርዳር ላይ በትግራይ ተወላጆች ግፍ እንዲፈፀም  የተደረገውን የማቀጣጠል ስራ ላይ ከፍተኛ ሚና ከነበራቸው መካከል በውጭ የሚገኙ ሚድያዎች ናቸው። እነሱም    የአሜሪክ ድምፅ የአማርኛ ክፍል፣ የጀርመን የአማርኛ ድምፅ፣ ዘሃበሻን ጨምሮ የተለያዩ ድህረ ገፆችን ያካትታል።  ኣሁንም ቢሆን እየሆነ ያለው ተመሳሳይ ነው። ሰሙኑን  በዛሃበሻ ድህረ ገፅ የሚተላለፈው መጣጥፎች እንደሚሉት  ወያኔ በአማራ ክልል ህዝብ እያሰቃዬ ነው ፣  ወያኔ ያልተፈለገ ግበር እየጫነ ነው፣ ወያኔ እናጠፋለን  ወዘተ በማለት የተለያዪ ቅስቀሳዎች በመደረግ ላይ ናቸው።  በዚህ ወሬም በባህርዳር ላይ ሙከራዎች እንደነበሩ የመንግስት ሚድያዎ ሳይቀሩ አስተጋብተዋል። ትንሽ የቀረው የወያኔ ኣገዛዝ መንግስት መግፋት ነው ያለብን ይላሉ።

በእርግጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት እነሱ ከሚያወሩት በጣም የተለየ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ይመስለኛል። ምንም ቢደረግ ምን ፣ ምንም ቢያጥላሉ ምን ፣

- የኣገራችን ኢኮኖሚው በፈጣን የእድገት መለክያ መሰረት እያደገ  መሆኑን የኣለም ኣቀፍ ተቅዋማት ሳይቀሩ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፣
- የከፉ ድርቅ ቢያጋጥመንም ያለንን ሃብት በመጠቀም ለድርቁ የተጋለጡ ወገኖቻችን እርዳታ እንዲያገኙና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን እየተገለፀ ነው፣
- ታላቁ የህዳሴ ግድባችንም በታለመለት መሰረት እየሄደ ነው
- ኣገራችን ቀጥታ የውጭ እንበስትመንትን በመሳብ ቀዳሚ ከሚባሉት የኣፍሪካ ኣገራት መካከል ኣንዷ ናት
- ዜጎች በሰላም የመኖርና ስጋት ባማከለ በኣፍሪካ በተደረገው ጥናት  ኢትዮጵያ ኣገራችን በሰላም የሚኖርባቸው ከተባሉት ኣምስት የኣፍሪካ  ኣገራት መካከል  ኣንዷ ሁናለች
- በኣጠቃላይ የኣገራችን `ኢኮኖሚ  ሲታይና ሲመዘን ባለፉት 26 ዓመታት ውስጥ ለ700 ዓመታት የነበረውን የኋሊዮሽ ጉዞ ኣስቁመን/ ተገትቶ በጤናማ ጉዞ ላይ መሆኑን እየተመሰከረ ባለበት ግዜ ላይ ነን ያለነው

እውነታው ይህ ሁኖ ሳለ  በዘሃበሻ ድህረ ገፅና መሰሎቹ  የሚሰራጨውን ዘገባዎች  ወስደንና  እነሱ እንደሚሉት ሊሆን የሚችለውን ያክል   ጥግ ድረስ ሂደን እንየው። ለምሳሌ  በኣማራ ክልል ያለው የክልልና የፌዴራል  የመንግስታት መዋቅር ፈርሶ  በኣማራ ህጋዊ የህግ ኣስከባሪ የሌላት ክልል  ትሁን ብለን እንውሰድ፣   ማነው የሚጎዳው? ይህ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት ይወድቃል ብላችሁ ታስባላችሁ?

> **እርግጠኛ ሁኙ የምናገረው ትግራይን የሚውክል ኣካል ያስፈልጋል። የትግራይ ህዝብ ዳግም ወደ ደርጋውያንና ኣፄዎቹ ኣስከፊ ስርዓት ለመመለስ ኣይፈልግም። ዳግም በጎንደርና በባህርዳር ያየውን ግፍና ጭካኔ ማየት ኣይፈልግም።  ዳግም በትግራይ ተወላጆች ውርደት የሚያፌዝ ኣካል ማየት ኣይፍለግም። ምን ግዜም ቢሆን የትግራይን ህዝብ ጠላቶች ከሆኑት ደርጋውያንና መሰሎቹን መታደግን ይፈልጋል። ነገር ግን የትግራይ ህዝብ እላፊ ከማንም ኣይፈልግም፣ ሰርቶ መብላት ግን ይፈልጋል፣ በሰላም መኖር ይፈልጋል፣ የሌላ መብት ኣይጋፋም። ራስን በራስ የማስተዳደርን መብት የሚነፍጉትን ኣይሻም። በመሆኑም    በስሙ ለመነገድ የሚሽቆጠቆጡም    ሆነ የሚቧጥጡ፣ እንዲሁም የሚያስፈራሩትን  ለመቀበል የሚችል  ጭንቅላት የለውም ብዬ ኣስባሎሁ ። ይህ እውነት ነው  ብዬ እወስዳሎህ**

ታድያ ከጥቃት ለመዳን/ለመታደግ/ መደራጀት ያስፈልጋል ።  መደራጀት ካስፈለገ ደግሞ  መሪ ያስፈለገውል። ይህንን ሃላፊነት ሊወጣ የሚችል ኣካል ማነው ብንል ኣንድ ነገር በኣእምሮኣችን ሊመጣ ይችላል ። በኣእምሮኣችን ሊመጣ የሚችለው ደግሞ  በኣሁኑ ሰኣት የትግራይን ህዝብ ድጋፍ ያልተለየውና  ጠንካራ ፓርቲ የምንለው  ህወሓት እንደሆነ ግልፅ ነው ። ከዚህ የምንረዳው   ምንም ቢሆን ምንም!  ወያኔ ሊወድቅ ኣይችልም ማለት ነው። ስለዚህ የኣማራ ጥቂት ሊሂቃን ነን ባዮችና የነሱን ሃሳብ ተከታዮች  የሆኑትን ጭምር ተስፋ መቁረጥ ያለባቸው ይመስለኛል።

ለዚህም ነው ቀደም ብዬ ወያኔን ከፍ የማድረግ ወይም ዝቅ የማድረግ ሙብት የትግራይ ህዝብ ሙብት ብቻ እንደሆነ የገለፅኩት ። የትግራይ ህዝብ ከፈቀደለት ወያኔ እስከወድያኛው ድረስ ሊዘልቅ ይችላል ። ማለትም በአማራ ክልል ውስጥ ሰላም ኖረ አልኖረ በወያኔ ህልውና ላይ ለውጥ እንደሌለው መገንዘብ ያስፈልጋል ብዬ አስባሎህ ። ይቅርና በአማራ ክልል ብቻ ፣ አዲስ አበባ ላይ ችግሩ ቢከሰትም በወያኔ ህልውና ላይ ለውጥ እንደሌለ መገንዘብ ያስፈልጋል እላሎህ። ምናልባት በዘሃበሻ ድህረ ገፅ ና መሰሎቹ እንደሚገለፁት በትእቢት ተወጥረው በመደራጀት የትግራይን ችግር ማየት የሚፈልጉ ወገኖች መፍትሄ ያመጣሉ ብለው የሚያሰቡ ከሆነ ሞኝነት ነው እላሎህ። የደርግን የመሸመድመድ ምስጢር በአስተማሪነቱ መውሰድ የሚቻል ይመስለኛል ። ስለዚህ ወያኔ በባህርዳር ላይ ስለ ጮሁ የሚለወጥ ነገር የለም ማለት ይቻላል ።

ጉዳዩ በአማራና በትግራይ ተንፅባረቀ እንጂ በሌላውም ክልሎችና ብሄረ ሰቦች ተሻጋሪ ሊሆን የሚችል ሃሳብ ነው ። በ2008ዓ/ም በጎንደር ላይ በነበረው ግርግር ተገደው የትግራይ ተወላጆች የክረምት ተማሪዎች የሆኑትን ከጎንደር ዩንቨርስቲ ወደ ትግራይ ሸሽተው መመለሳቸው ይታወቃል። በዚህ ወቅት የትግራይ ተወላጆች ሲሸሹ አንዳንድ የሌላውም ብሄር እንደሸሹም ይነገራል። አንድ ተማሪ የነገረኝን ላውራችሁ፣

> ለናንተ ቁርስ ካደረጉ ለኛ ራት ሊያደርጉን ይችላሉ ብሎ አንድ የኦሮሞ ተወላጅ ከጎንደር ሸሰቶ እንደሄደ አጫውተውኛል ።

በአንዳንድ የአማራ ሊሂቃን ነን ባዮች አንድን ብሄር በማንነቱ ብቻ የሚያካሂዱት ዘመቻ በኢትዮጵያ ውስጥ በየተኛውም ብሄር ብሄረሰቦች ተቀባትነት ይኖረዋል ብዬ አላስብም። የግዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አንዱን በማንነቱ ብቻ ጠልተህ ሌላውን ወዳጅ ማድረግ የስትራትጂካዊ መርህ ነው ብየ አስባሎህ ። ነገር ግን መሰረታዊ ባህርይን አይቀይርም ። ከተሳካላቸውና ከተመቻቸላቸው ግዜውን ጠብቆ የወደድቱንም ቢሆን መዋጣቸው አይቀርም ። ምክንይቱም ባህርይ ባህርይ ነውና። ባይሆን ኑሮ በትግራይ ተወላጆች በጎንደርና ባህርዳር የደረሰው ግፍ ቢያንስ ሊያሳዝናቸው በተገባ ነበር። ስለዚህ ከዚህ የምንረዳው፣ ከአንዳንድ የአማራ ሊሂቃን ነን ባዮችና በአስተሳሰባቸው የተመረዙ ሰዎች በስተቀር የአሁኑ የኢህዴግ መርህ፣ በመርህ ደረጃ የማይቀበለው አለ ብዬ አላሳብም ። ልዩነት የሚኖረው በኢህዴግ ውስጥ የሚታየው የአሰራር ብልሹነትን ያለማስተካከል ጉዳይ ነው ። በመሆኑም አንዳንድ የአማራ ሊሂቃን ነን ባዮች በውሸት የሚቋምጡትንና የሚሰነዝሩትን ሃሳብ በየተኛውም ብሄር ብሄረ ሰብ ጋር አብሮ መጓዝ የማይችል የነቀዘ አስተሳሰብ ነው ለማለት ይቻላል ። የነዚህን ሊሂቃን ነን ባዮች አስተሳሰብ ገላጭ ይሆናል ያልኩትን በፊስ ቡክ የተለጠፈውን ላጋራችሁ፣

መንፈሴ በባህዩ ይላል ርእሱ

- አንድነት ይላል። በተግባር ግን አንድ-አይነትነት
- ሃገር ወዳድ ይላል=በተግባር ግን ሃገር ሻጭነት ነው
- ሁላችን ይላል=በተግባር ግን አግላይ ነው
- ፍቅር ይላል። በተግባር ግን ጥላቻ ነው
- አትከፋፍሉን ይላል=በተግባር ግን ከፋፋይ ነው
- ኢትዮጵያዊነት ይላል= በተግባር ግን እኔን -ሁን ነው

- ሃገራዊ መንፈስ ይላል= በተግባር ግን ሃገራዊ ክሽፈት ነው
- ዘር የለም ይላል= በተግባር ግን ዘረኛ ነው
- መዋደድ ይላል = ነገር ግን መነታረክ ነው
- ታሪክ ይላል = በተግባር ግን ትርክት ነው

ከዚህ ግጥም መሰል ፅሁፍ ብዙ መልእክት ያዘለ ይመስለኛል። ለእንደነዚህ ኣይነት ሰዎች ምን ማለት እንዳለብንም ደግመን ደጋግመን ማሰብ ያስፈልጋል።

ስለዚህ ከላይ የተገለፀውን ሁኔታ የሚያሳየው ነገር ኣለ። ከሁሉም በላይ መገንዘብ ያለብን በኢትዮጵያ ያለው የፌዴራል ስርዓት ኣንድ ጫፍ ብቻ ስለተነካ ተርመስምሶ የሚወድቅ ስርዓት ኣለመሆኑን ነው። ይልቁንስ ለጋራ ብልፅግና፣ በጋራ የተጠቃሚነት መርህ ተመስርተን በውይይት ና በመቻቻል ኣብሮ መኖርን ብናጎለብት ለሁላችንም የሚጠቅመን ይመስለኛል። ካልሆነ ግን ዳግም በ 1270ዓ/ም ኣካባቢ የተፈበረከው የኣማራ ገዢ መደቦች የበላይነትን በሌላ ህዝብ የመጋት ኣባዜን መቀበል ውርደት ነው። እንደ ትግራይ፣ እንደ ሶማሌ ፣ እንደ ኦሮሞ፣ እንደ ኣማራ፣ እንደ ኣፋር እንደ ደቡብ ህዝቦች ራሳችን በራሳችን መብት እንዲኖረን እንፈልጋለን። ኢትዮጵያ የጋራችን እንጂ የእናውቅላሃለን ባዮች ብቻ ኣይደለችም። ኣመሪካ ሁኑ በሚያዘምተው ቡድን ባህርዳር ላይ ሁኖ የትግራይ ወኪል እናጠፋለን ማለት በ 21 ክፍለ ዘመን የማይጠበቅ ነው። መታወቅ ያለበት የሌላውን መብት ተጋፍቶ እኔ ኣውቅላሃሎህ በሚል ኣላስፈላጊና የማያዛላቅ ትርክት መግባትና የጥላቻ ፖለቲካ ማራገብ የኣእምሮ ዝቀት የፖለቲካ ትርክት ካልሆነ ምን ይባላል??